መልእክት ስምንት

## በማደሉ የሆነው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ በኤርሚያስ መጽሐፍ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 2፡13፤ 15፡16፤ 17፡7-8፣ 19-27፤ 23፡5-6፤ 31፡31-34፤ ዕብ. 8፡8-12

**I. ኤርሚያስ 17፡7-8 እንዲህ ይላል፣ "በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው። በውኃ አጠገብ እንደተተከለ፣ በወንዝም ዳር ሥሩን እንደሚዘረጋ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ ቅጠሉም እንደሚለመልም፣ በድርቅ ዓመትም እንደማይሰጋ ፍሬውንም እንደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል"፦**

ሀ. እነዚህን ጥቅሶች በሁለት የተለያዩ መንገዶች ልንረዳ እንችላለን—በፍጥረታዊው መረዳት መሠረት ወይም በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መሠረት፤ እነዚህ ጥቅሶች ቁሳዊ በረከቶችን ለመቀበል ላይ ላዩን በሆነ በእግዚአብሔር የመታመን ጉዳይ ላይ ያተኮሩ አይደሉም፤ በእውነቱ እነዚህ ጥቅሶች የሚያመለክቱት በማደሉ የሚከናወነውን የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ነው።

1. እዚህ ያለው መገለጥ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መሠረት፣ በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው በውኃ አጠገብ እንደተተከለው ዛፍ እንደሆነ ይገልጣል፣ ይህም [ውኃ] እግዚአብሔርን እንደ የሕያው ውኃ ምንጭ ያመለክታል (2፡13)፤ እኛ በእግዚአብሔር የምንታመን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ በእርሱ ላይ ያለን መታመናችንም ጭምር ነው።
2. ዛፉ የውኃውን ብልጥግናዎች ሁሉ ወደ ውስጡ በመምጠጥ በውኃው አጠገብ ያድጋል። ይህ የእግዚአብሔር ማደል ስዕል ነው፤ መለኮታዊውን እደላ ለመቀበል ዛፎቹ እንደሚያደርጉት፣ ቅንብራችን ይሆን ዘንድ ወደ ማንነታችን ውስጥ እንዲታደል እንደ ሕያው ውኃ እግዚአብሔርን መምጠጥ አለብን።

ለ. እዚህ ጋር ያለው ሀሳብ በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡6 ውስጥ፣ ጳውሎስ "እኔ ተከልሁ አጵሎስ አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ማጠጣቱ ዛፉ እንዲመጥጠው ነው፣ መምጠጡ ደግሞ የእግዚአብሔርን እደላ መቀበል ነው፡-

1. ዛፉ አቅራቢና አቅርቦት በሆነው በእግዚአብሔር ያድጋል፤ አቅርቦቱ ወደ እግዚአብሔር ልክ እናድግ ዘንድ እንደ ተክሎቹ አቅርቦት የሚሰጠው የእግዚአብሔር ብልጥግናዎች ወደ እኛ ውስጥ መታደሉ ነው፤ በመጨረሻም፣ ተክሎቹ እና እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር እና ተክሎቹ፣ አንድ ንጥረ-ነገር፣ ውስጠ-ነገር፣ ቅንብር እና መልክ ያላቸው በመሆን አንድ ይሆናሉ—ቆላ. 2፡19።
2. በእርሱ ንጥረ-ነገር እና ውስጠ-ነገር እንድንቀናበር እና በእግዚአብሔር እድገት እንድናድግ እግዚአብሔርን እንደ ሕያው ውኃ የመምጠጥን ወሳኝ አስፈላጊነት ሁላችንም ማየት ያስፈልገናል፤ የሕይወት እድገት እጥረት በሚኖርበት ቦታ የአማኞች የክርስትና ሕይወት የተመሰቃቀለ ይሆናል፣ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ይጎዳል፣ የአካሉም ሕይወት ይጠፋል።
3. ለክርስቶስ አካል ግንባታ በሕይወት ለማደግ፣ ወደ ታች ሥር በመስደድና ወደ ላይ ፍሬን በማፍራት እግዚአብሔርን መምጠጥ አለብን (ኢሳ. 37፡31)፤ ይህ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር የተሰወሩ የኅብረት ጊዜዎች ሊኖሩን ያስፈልጋል ማለት ነው (ማቴ. 6፡6፤ 14፡22-23)፤ ለክርስቲያን ኃይል ማግኘት፣ አብርሆት መቀበል፣ እረፍትን መደሰት፣ ሐሴት ማድረግ፣ ማመን፣ የችግሮች መፈታት፣ ፈተናዎችን እና መከራዎችን ማሸነፍ፣ እንዲሁም መጽናናት ሁሉም የሚመረኮዙት በጸሎት እና በእግዚአብሔር ቃል በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ባለው የምሥጢር ኅብረት ላይ ነው (ዳን. 6፡10፤ ቆላ. 4፡2፤ 2 ጢሞ. 3፡14-17)።

**II. በኤርሚያስ 17፡19-27 የእግዚአብሔርን ሰንበት ስለ መጠበቅ ቃል አለን፤ የእግዚአብሔርን ሰንበት የመጠበቂያው መንገድ እርሱን መደሰት፣ በእርሱ ማረፍ እና እንደ ሕይወት ውኃዎች ምንጭ በእርሱ መርካት ነው—2፡13፦**

ሀ. ስለ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ መገንባት ከተሰጠው ረጅም ዘገባ በኋላ፣ በዘጸአት 31፡12-17 ሰንበትን ስለ መጠበቅ ተደጋጋሚ ትእዛዝ አለ፤ በቆላስይስ 2፡16-17 እና በማቴዎስ 11፡28-30 መሠረት፣ ክርስቶስ የሰንበት እረፍት እውነታ ነው—ዕብ. 4፡7-9፤ ኢሳ. 30፡15፦

1. ለጌታ እንዴት መሥራት እንዳለብን ብቻ የምናውቅ ነገር ግን ከእርሱ ጋር እንዴት ማረፍ እንዳለብን የማናውቅ ከሆንን፣ ከመለኮታዊው መርህ በተቃራኒ እየተንቀሳቀስን ነው፦

ሀ. እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ያረፈው ሥራውን ስለጨረሰ እና ስለረካ ነበር፤ የእግዚአብሔር ክብር የተገለጠው ሰው የእርሱ መልክ ስለነበረው እና ለጠላቱ ለሰይጣን ተረግጦ መገዛት የእርሱ ስልጣን መንቀሳቀስ ሊጀምር

ስለነበረ ነው፤ ሰው እግዚአብሔርን እስከገለጠ እና የእግዚአብሔርን ጠላት እስካስወገደ ድረስ፣ እግዚአብሔር ረክቷል ማረፍም ይችላል—ዘፍ. 1፡26፣ 31፤ 2፡1-2።

ለ. ኋላም፣ ሰባተኛው ቀን እንደ ሰንበት መታሰቢያ ሆነ (ዘጸ. 20፡8-11)፤ የእግዚአብሔር ሰባተኛው ቀን የሰው የመጀመሪያ ቀን ነበር፤ ሰው ከተፈጠረ በኋላ በእግዚአብሔር ሥራ አልተሳተፈም፤ ወደ እግዚአብሔር እረፍት ውስጥ ገባ።

2. ሰው የተፈጠረው በመጀመሪያ እንዲሠራ ሳይሆን ነገር ግን በእግዚአብሔር እንዲረካ እና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያርፍ ነበር፤ ለእግዚአብሔር የመሥራት እና የማረፍ ጉዳይ ነው፣ ለሰው ግን የማረፍ እና የመሥራት ጉዳይ ነው፤ እግዚአብሔርን በሙላት ከመደሰት በኋላ፣ ከእርሱ ጋር አብረን መሥራት መቻላችን መለኮታዊ መርህ ነው—ተዛ. ማቴ. 11፡28-30፦

ሀ. እግዚአብሔርን ራሱን እንዴት መደሰት እንዳለብን እና በእግዚአብሔር እንዴት መሞላት እንዳለብን ካላወቅን፣ ከእርሱ ጋር እንዴት መሥራት እንዳለብን እና በመለኮታዊው ሥራው ውስጥ ከእርሱ ጋር እንዴት አንድ መሆን እንዳለብን አናውቅም፤ ሰው እግዚአብሔር በሥራው የፈፀመውን ይደሰታል።

ለ. በበዓለ ኃምሳ ቀን ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ተሞሉ፣ ይህም ማለት እንደ ሰማያዊው ወይን ጠጅ በክርስቶስ ድሰታ ተሞሉ ማለት ነው፤ በዚህ ድሰታ ከተሞሉ በኋላ ብቻ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሆነው መሥራት ጀመሩ—ሐዋ. 2፡4፣ 12-14።

ሌ. እንደ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የምናርፍ፣ እግዚአብሔርን የምንደሰት እና በመጀመሪያ በእግዚአብሔር የምንሞላ መሆናችንን የሚያሳይ ምልክት ሊኖረን ይገባል፤ ከዚያም በሚሞላን በእርሱ እንሠራለን፤ በተጨማሪም የምንሠራው ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ በመሆን ጭምር ነው፣ ይህም እርሱ ለመሥራት እንደ ብርታታችን እና ለመድከም እንደ ጉልበታችን እንዲሆንልን ነው—31፡13፣ 17።

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መጀመሪያ ጌታን ሳንደሰትና ከጌታ ጋር አንድ በመሆን ጌታን ሳናገለግል ብዙ ነገሮችን ልናደርግ እንችላለን፤ እንደዚያ ዓይነቱ አገልግሎት መንፈሳዊ ሞትን እና በአካሉ ውስጥ ያለውን ኅብረት ማጣትን ያስከትላል—ቁ. 14-15።

መ. ቤተ ክርስቲያንን መገንባት የሆነው የጌታ ሥራ እግዚአብሔርን በመደሰት መጀመር አለበት፣ ይህም እርሱን በመደሰትና ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን እንጂ በራሳችን ብርታት ለእግዚአብሔር እንደማንሠራ የሚያመለክት ይሆናል፤ ይህ በመንፈሳችን ውስጥ እንዳለው ውስጣዊ እረፍት በክርስቶስ የሰንበትን መርህ መጠበቅ ነው—1ቆሮ. 3፡9፤ 15፡58፤ 16፡10፤ 2ቆሮ. 6፡1።

**III. የኤርሚያስ መጽሐፍ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ አህጽሮተ ጽኑፍ (abstract) ነው፤ የኤርሚያስ ትንቢት የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ መፈጸም የሚችለው ክርስቶስ ብቻ መሆኑን እና በኢኮኖሚው ውስጥ ለእግዚአብሔር ጥያቄዎች ክርስቶስ ብቻ መልስ መሆኑን ነው፤ በኤርምያስ የተመለከተው ስዕል እኛ ምንም እንደሆንን እና ክርስቶስ ለእኛ ሁሉንም ነገር እንደሆነ ያሳያል፦**

ሀ. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም ውስጥ ክርስቶስ ጽድቃችን እና ቤዛነታችን ስለመሆኑ (23፡5-6)፣ እግዚአብሔር የሕያው ውኆች ምንጭ ስለመሆኑ (2፡13)፣ ክርስቶስ ምግባችን ስለመሆኑ (15፡16)፣ እና ከበረከቶቹ ሁሉ ጋር የአዲሱ ኪዳን እውነታ ክርስቶስ ስለመሆኑ (31፡31-34፤ ዕብ. 8፡8-12) ኤርሚያስ ይናገራል።

1. በአንድ በኩል፣ አዲሱ ኪዳን የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ይዘቶችና ንጥረ-ነገር በመሆን ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር ተመሳሳይ ትርጓሜ አለው ማለት እንችላለን—ኤር. 31፡31-34፤ ኢዮ. 10፡13፤ ተዛ. ኤፌ. 3፡9፦

ሀ. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለምትጠናቀቀው ለክርስቶስ አካል መገንባት እኛን መለኮት ለማድረግ ከፍተሃዊ ቤዛነቱ እና ከሕይወታዊ ማዳኑ ጋር የአዲሱ ኪዳን ዋና ዋና ነገሮች ሁሉ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ እና የእደላው ይዘቶች ናቸው።

ለ. የሐዋርያቱ አገልግሎት ለእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ የሆነ አገልግሎት ነው፤ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚን ማዕከል ያደረገ የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት ነው—1 ጢሞ. 1፡3-4፤ ተዛ. 2 ቆሮ. 3፡3፣ 6።

2. በሌላ በኩል፣ አዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር ኢኮኖሚውን የሚፈጽምበት ወይም የሚያከናውንበት መንገድ ነው ማለት እንችላለን፤ 2ኛ ቆሮንቶስ የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መፈጸም መሆኑን ይገልጣል—2፡12—4፡1።

ለ. ክርስቶስ የአዲሱ ኪዳን፣ የአዲሱ ቃል ኪዳን እውነታ ነው፣ እግዚአብሔር የሆነው ሁሉ እና እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ሁሉ እውነታ ነው፤ ስለዚህ ክርስቶስ አዲሱ ቃል ኪዳን ነው፦

1. የኑዛዜዎቹ ውርሶች ብዙ ናቸው፣ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ በርካታ ውርሶች በእውነቱ አንድ ማንነት—እስትንፋሳዊው ክርስቶስ—ነው—ኢሳ. 42:6፤ 49:8፤ ኤር. 31:31-34፤ ዕብ. 8:8-12፤ ዮሐ. 20:22፤ ኤፌ. 3:8።
2. በአዲሱ ኪዳን በጌታ በኑዛዜ የተሰጡን ውርሶች ማለቂያ የላቸውም፣ በመንፈስ በኩል ለዘላለም እንድንለማመዳቸው እና እንድንደሰታቸው ናቸው—ዕብ. 9:15።
3. ወደ ሕይወት በሚወስደው፣ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ላይ ባተኮረው በአዲሱ ኪዳን መንገድ በመመላለስ የአባቶቻችንን ጥንታዊ ጎዳና መውሰድ አለብን፤ ከዋናው ጎዳና ውጪ ያሉ መንገዶች ወደ ጥፋት የሚያደርሱ በተንኮለኛ ስልቶቹ መሠረት የሆኑ የሰይጣን የሴራ መንገዶች ናቸው፤ ከዋናው ጎዳና ውጪ ያሉ መንገዶችን መውሰድ ቁልቁል መውረድ ነው፣ ነገር ግን የጥንቶቹን ጎዳናዎች፣ ወደ ላይ የተሠራውን መንገድ መውሰድ ወደ ላይ መውጣት ነው—ኤር. 18:15፤ ተዛ. ማቴ. 7:13-14።
4. በአዲሱ ኪዳን፣ በዘላለማዊው ኪዳን፣ እግዚአብሔር አንድ ልብ እና አንድ መንገድ ይሰጠናል (ኤር. 32:39-41)፤ አንዱ ልብ የእርሱ መገለጥ እንሆን ዘንድ እግዚአብሔርን ለመውደድ፣ እግዚአብሔርን ለመፈለግ፣ እግዚአብሔርን ለመኖር እና በእግዚአብሔር ለመቀናበር የሆነ ልብ ነው፣ አንዱ መንገድ ሦስታንዱ አምላክ ራሱ እንደ ውስጣዊው የሕይወት ሕግ ከመለኮታዊው አቅም ጋር ነው (31:33-34)፤ ይህ አንድ ልብ እና አንድ መንገድ በአንድ ልብ መሆን ናቸው (ሐዋ. 1:14፤ 2:46፤ 4:24፤ ሮሜ 15:6)።

ሐ. በአዲሱ ኪዳን ያሉትን የውርስ ኑዛዜዎች ሁሉ እንድንገነዘብ፣ እንድንለማመድ እና እንድንደሰት ለእኛ በመማለድና በማገልገል በሰማይ በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠው እንደ ዐረገው ማንነት፣ ክርስቶስ አሁን እንደ ኑዛዜ ለእኛ ያወረሰንን አዲሱን ኪዳን እየፈፀመ ነው—ዕብ. 12:2፤ 7:25፤ 8:1-2፦

1. አዲሱ ኪዳን፣ አዲሱ ቃል ኪዳን፣ ኑዛዜው፣ በክርስቶስ ሞት ተረጋግጧል እንዲሁም በትንሣኤው እና በዕርገቱ በክርስቶስ እየተፈጸመ ነው።
2. አዲሱ ኪዳን እንደ አዲሱ ቃል ኪዳን በኑዛዜ የእኛ ውርስ ሆኗል፣ እናም አሁን፣ በሰማያዊ አገልግሎቱ ምሥጢራዊ ክልል ውስጥ፣ ክርስቶስ በኑዛዜ ያወረሰንን እየፈፀመ ነው።
3. ክርስቶስ አሁን በሰማይ ያለ፣ ሕያው፣ መለኮታዊ እና ብቃት ያለው ነው፤ እርሱ አዲሱን ኪዳን፣ በዝርዝር ሊፈጽም፣ በአዲስ ኪዳኑ የወረስነውን ሁሉ ለእኛ እውን እና በቀላሉ የሚገኝ ለማድረግ ብቁ ነው፦
   ሀ. እንደ መለኮታዊ ሊቀ ካህን፣ ክርስቶስ ወደ አዲሱ ኪዳን እውነታ እንድንገባ በመጸለይ እየማለደልን፣ አዲሱን ኪዳን እየፈፀመ ነው—7:25።
   ለ. የአዲሱ ኪዳን መካከለኛ እና አስፈፃሚ እንደመሆኑ ክርስቶስ በሰማያዊ አገልግሎቱ አዲሱን ኪዳኑን እየፈፀመ እና ውርሶቻችንን ሁሉ በእኛ ውስጥ እያከናወናቸው ነው—8:6፤ 9:15፤ 12:24።
   ሐ. እንደ አዲሱ ኪዳን ዋስ፣ ክርስቶስ በአዲሱ ኪዳን ውስጥ ያለው ሁሉ የሚፈጸምበት የኪዳን መያዣ ነው፤ እርሱ የአዲሱን የኪዳን ውጤታማነት ዋስትና ይሰጣል ያረጋግጣልም—7:22።
   መ. እንደ የእውነተኛው (ሰማያዊ) ድንኳን አገልጋይ የአዲሱን ኪዳን ሀቆች በልምምዳችን ፍቱን እንዲሆኑ በማድረግ ክርስቶስ በአዲሱ ኪዳን ውርሶች፣ በረከቶች እያገለገለን ነው— 8:2።
   ሠ. እንደ ታላቁ የበጎች እረኛ፣ ክርስቶስ፣ በእረኝነት እንክብካቤው፣ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኪዳን መሠረት አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን እያጠናቀቀ ነው—13:20።

መ. በአዲሱ ኪዳን ውስጥ ያሉትን በረከቶች ሁሉ ጥቅም እንድንቀበል ለክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ምላሽ የሚሰጡ ሰዎች መሆን ያስፈልገናል—12:1-2፤ ቆላ 3:1፦

1. በሰማያት ያለው የክርስቶስ አገልግሎት አዲሱን ኪዳን ለመፈፀም ምላሻችንን ይጠይቃል—ዕብ. 7:25፤ 4:16፤ 10:19፤ 22፦
   ሀ. ክርስቶስ ያለበቂ ስኬት ለምዕተ ዓመታት በሰማያት ላለው አገልግሎቱ ምላሽ የሚሰጡ የሰዎችን ቡድን ለማግኘት ሲሞከር ቆይቷል።
   ለ. በጌታ ምሕረት እና ጸጋ፣ ዛሬ በምድር ላይ ለክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ምላሽ የሚሰጡ የሰዎች ቡድን በጌታ ምለሳ ውስጥ አሉ።
   ሐ. ራስ የሆነው በሰማይ ለእኛ ሲማልድና ሲያገለግል ሳለ፣ እኛ አካሉ እርሱ አዲሱን ኪዳን ለመፈፀም ከሚያደርገው ነገር ጋር በመዛመድ እና በማንጸባረቅ በምድር ለክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ምላሽ እየሰጠን ነው—ኤፌ. 1:22-23፤ 4:15-16፤ ሐዋ. 6:4።
2. የአዲሱን ኪዳን፣ የአዲሱን ቃል ኪዳን፣ ከውርሶቹ ሁሉ ጋር የኑዛዜውን ሰማያዊ ራእይ ለማየት ዓይኖቻችን መከፈት አለባቸው—ኤፌ. 1:17-18፤ ሐዋ. 26:18-19፦

ሀ. አብ ሁሉን ነገር ቃል ገባ፣ ጌታ ኢየሱስም ሁሉን ነገር ፈጸመ፤ አሁን የተፈጸሙት ሀቆች ሁሉ እንደ ውርሶቻችን በኑዛዜው ውስጥ ተዘርዝረዋል—ሉቃ. 22፡20፤ ዕብ. 9፡16-17።

ለ. የእግዚአብሔር በረከቶች ሁሉ በኑዛዜ ውስጥ ያሉ ውርሶች መሆናቸውን ለማየት ሰማያዊ ራእይ ካለን፣ ውርሶቹን በእምነት በመቀበል እንደ ምስኪን ለማኞች ሳይሆን እንደ ክቡር ወራሾች እንጸልያለን—ሮሜ 8፡17፤ ኤፌ. 3፡6፤ ዕብ. 6፡17፤ 1፡14።

ሐ. የአዲሱ ኪዳን፣ የአዲሱ ቃል ኪዳን ሰማያዊ እይታ ካለን፣ ጽንሰ-ሃሳባችን ይለወጣል፣ ስር-ነቀል በሆነ ሁኔታ እንለወጣለን እንዲሁም ጌታን በማመስገን በደስታ ከራሳችን ውጪ እንሆናለን—2 ቆሮ. 5፡13፤ ራእ. 5፡6-13።

ሠ. ኤርሚያስ 31፡31-34ን ለማብራራት ሀያ ሰባቱም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ያስፈልጉናል፦

1. ይህንን ክፍል በመላው የአዲስ ኪዳን ብርሃን ብንረዳ፣ በዚህ አዲስ ኪዳን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ፣ በመንፈሳችን ውስጥ እንዳለው የእግዚአብሔር መኖሪያ የእግዚአብሔር ቤት፣ አዲሱ ሰው፣ እና በሂደት እንዳለፈውና እንደተጠናቀቀው ሦስታንድ አምላክ ሙላት የክርስቶስ አካል እንዳለን እናያለን።

2. በመጨረሻ፣ ይህ አዲስ ኪዳን የአንድ ሺሁን ዓመት ያመጣል፤ በከፍተኛና የመጨረሻ ድምዳሜው እና በመጠናቀቁ አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን በአዲስ ሰማይና በአዲሱ ምድር ለዘላለም ያመጣል።

*© 2020 Living Stream Ministry*